## የሰሜን ሸዋ ጭፍጨፋና የኦነግ ሸኔ ጉዳይ፣ ያልተመለሱ ጥያቄዎች
## ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተሰጠ መግለጫ

**ሚያዝያ 14 ቀን 2013 ዓ. ም**

ባለፉት ተከታታይ ቀናት በሰሜን ሸዋ ውስጥ ከባድ መሣሪያ የታጠቀ ኃይል ባካሄደው ጥቃት ሕይወታቸው ለጠፋ ቤታቸውና ንብረታቸው ለወደመና እንዲሁም ዕድሜ ልካቸውን ተወልደው ካደጉበት አገር "መጤ" የሚል አስነዋሪ የሆነ ስም እየተሰጣቸው ለተፈናቀሉ ወገኖቻችንና እንዲሁም በትግራይ፣ በመተከል፣ በማይካድራና በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች ሁሉ በግፍና በአሰቃቂ ሁኔታ በጅምላ ለተገደሉ ወገኖቻችን ኢሕአፓ የተሰማውን ከፍተኛ ሃዘን ይገልጻል።

በሰሜን ሸዋ በመንግሥት ባለሥልጣናትና በአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚነገረው ጥቃቱን ያደረሰው ኦነግ ሸኔ የሚባል ቡድን መሆኑና ጥቃቱም ያነጣጠረው በአማራ ማኅበረሰብ አባላት ላይ እንደሆነ ነው። ይህ በአማራው ማኅበረሰብ አባላት ላይ በተለያዩ ጊዜያትና አካባቢዎች አሁን ደግሞ በሰሜን ሸዋ የተፈጸመው ኢ-ሰብዓዊ ጭፍጨፋ አስከፊ፣ ከኢትዮጵያዊ ባሕሪ የወጣ ተግባር መሆኑን እንድንገልጽና ብዙ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያስገድደናል።

እንደሚታወቀው፣ ሰሜን ሸዋ የሀገራችን መሃል አገር ነው። በዋናነት የሚነሳው ጥያቄ እንዲህ ዓይነት እኩይ ተግባራትን በመከላከል የነዋሪውን ሰላማዊ ኑሮ የማረጋገጥ ዋነኛ ኃላፊነት ያለው ማዕከላዊ መንግሥት የት ነበር? ኦነግ ሸኔ በርካታ የታጠቀ ኃይል ይዞ መሃል አገር እስኪደርስ ድረስ የፀጥታ ኃይሉና የአካባቢው አስተዳደር ምን እያደረገ ነበር? ከየትም ይምጣ ከየት ይህ ኃይል ካራቆሬ ወይም ከሚሴ እስኪደርስ ብዙ መጓዝ አለበት። በዚህ ሁሉ ጊዜ እንዴት የአስተዳደርና የፀጥታ ኃይሉ ሊያስቆሙትና እርምጃ ሊወስዱበት አልቻሉም? ከአንድ መንደር ወደ ሌላ ሠፈር ለሚሄድ ሰላማዊ ዜጋ ስንት ግልምጫ በሚደርስበት በአሁኑ ወቅት፣ ቁጥጥሩ እንዴት በኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አልቻለም? ይህ ሁኔታ በእውቅ የተደረገ ይሆን እንዴ? እንድንልም አድርጎናል፡፡ ቀደም ሲል ተደጋጋሚና ተመሳሳይ ግጭት በተከሰተበት በሰሜን ሸዋ ኦነግ ሸኔ ወደ ተጠቀሱት ቦታዎች ከነተሸከርካሪዎቹና ታጣቂ ኃይሉ እንዴት ምንም ተቃውሞ ሳይገጥመው ማለፍ ቻለ? የፀጥታውን ሁኔታ ችላ ብሎ መንገድ ከፍቶ ያሳለፈው ማን ነው? የኦነግ ሸኔ የፀጥታ ኃይሉንና አስተዳደሩን እየደመሰሰ ነው መሃል አገር የደረሰው? ወይንስ ይህ ኃይል የተደራጀውም፣ የሰለጠነውም እዚያው ሰሜን ሸዋ የኦሮሞ ልዩ ዞን ውስጥ ነው? እነዚህ መመለስ የሚገባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄዎችን ሳይመልሱ፣ ኦነግ ሸኔ ይህን ጥቃት አደረሰ፣ እንዲህ ዓይነት አረመኒያዊ ተግባር ፈጸመ የሚል ተደጋጋሚ መግለጫ ማውጣት ምንም ትርጉም አይሰጥም፣ እንዲያውም ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን ያጭራል።

ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com

ጥያቄው በሰሜን ሸዋ ብቻ የተከሰተ አይደለም። በሀገራችን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች እየተካሄዱ ያሉት ጭፍጨፋዎች መቆም አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ኃላፊነቱ በዋናነት የማዕከላዊ መንግሥት ነው። መንግሥት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳትና ልዩ ትኩረት በመስጠት ሕዝብንና የአንድነት ኃይሉን አስተባብሮ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል። ይህ ተግባር የማዕከላዊ መንግሥት የሕግ የበላይነትን የማስከበርና የሁሉን ዜጋ በሰላም እንዲኖር የማስቻል ዋነኛ ኃላፊነቱ ነውና፡፡ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ እጅግ አንገብጋቢና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ችግሩም መሠረታዊ በመሆኑ አካባ ሸኔን በማውገዝ ብቻ የሚፈታ አይደለም። ለዚህ ሁሉ የዘር ፍጅት በህገመንግስት የተደገፈው በዘር ላይ የተመረኮዘው የፌደራል አወቃቀርና እራሱ ህገመንግሥቱ ሆነው ሳለ በእየቦታው የሳት መጥፋት ዘመቻና ኮማንድ ፖስት ማቋቋም ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም። መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋል፡፡ ችግሩን ለአንዴና ለሁልጊዜ ለመፍታት አግባብ ያለው ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ የግድ ነው።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ውስጥም የተካሄደው ከአምስት ወራት በላይ ያስቆጠረው ጦርነት የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት ቀጥፏል፣ ለስደት ዳርጓል፣ መፈናቀልን አስከትሏል። በጦርነቱ መሠረተ-ልማቶች ወድመዋዋል። በህወሓት እኩይ ተንኮል በሕዝባችን መሃል ልዩነትንና ጠላትነት የፈጠረው ሁኔታ አሁን በትግራይ እንዲሁም በበርካታ የሃገራችን ክፍሎች ተዛምቶ ያገራችንን የግዛት አንድነትና የሕዝባችንን ወንድማማችነት ከፉኛ እየፈተነው ይገኛል። እንዲሁም አሁን ሕዝቡ ላለበት አስከፊ ሁኔታ የዳረገው በህወሓት የተጫረው ጦርነት የትግራይ ሕዝብ መከራውንና ፍዳውን እንዲያይ አድርጎት ይገኛል። የትግራይ ሕዝብ ሰላማዊ ኑሮውን ለመቀጠል እንዲችል ለኑሮ የሚያስፈልጉ ማናቸውም ነገሮች እንዲሟሉለት ያስፈልጋል፣ ይህም ኃላፊነት የማዕከላዊ መንግሥት መሆኑን ማሳወቅ በመግለጽ እየተደረገ ያለውም ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። የትግራይን ሕዝብ ለዚህ የዳረገው ህወሓት ዳግም እንዳያንሰራራ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአንድነት በመታገል የትግራይ ሕዝብ እፎይታ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባናል። ለዚህም መንግሥት ወንጀለኞችን አድኖ ወደ ሕግ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት እንደግፋለን፣ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም እናሳስባለን።

የሰሜን ሸዋም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኘው ሕዝባችን በዚህ ዓይነት ተደጋጋሚ ጥቃት ሥር መኖር ከቶውንም የለበትም። ሕዝብ በሰላም የመኖር መሠረታዊ መብቱ መከበር አለበት። ለዚህም የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ የመንግሥት ዋነኛ ግዴታው ነው። መሠረታዊ የሆነውን የሕዝብን በሰላም የመኖር መብት የማስፈጸም ግዴታውን የማይወጣ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ መንግሥታዊ አካልም ተጠያቂ ሊሆን ይገባል።

ስለዚህ በሰሜን ሸዋና በሌሎችም አካባቢዎች የተፈጠሩትን ጭፍጨፋዎች በገለልተኛ አካል በአስቸኳይ እንዲጣሩና ወንጀለኞች ለሕግ እንዲቀርቡ እንዲደረግ ኢሕአፓ አጥብቆ ይጠይቃል።

ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር